የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፷፩
አዲስ አበባ ሚያዚያ ፳፬ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

22nd Year No 61
ADDIS ABABA 2nd May, 2016

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፱፻፵፪/፪ሺ፰ ዓ.ም

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር መወሰኛ (ማሻሻያ) አዋጅ…………………………………………………………..ገጽ ፰ሺ፱፻፷፬

## CONTENTS

Proclamation No.942 /2016

Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia (Amendment) Proclamation ………………….Page 8964

### አዋጅ ቁጥር ፱፻፵፪/፪ሺ፰

**<u>የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ</u>**

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግስት አንቀጽ ፶፭ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር መወሰኛ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፱፻፵፪/፪ሺ፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>ማሻሻያ</u>**

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፮/፪ሺ፯ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

### PROCLAMATION No. 942/2016

**<u>A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE AMENDMENT OF THE DEFINITION OF POWERS AND DUTIES OF THE EXECUTIVE ORGANS OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA</u>**

WHEREAS, it has become necessary to amend the Proclamation Defining the Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia (Amendment) Proclamation 942/2016".

**2. <u>Amendment</u>**

The Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation 916/2015 is hereby amended as follows:

፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፲፬ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (በ) እና (ተ) ተሠርዘው ቀጥለው ያሉት ፊደሎች (ቸ)፣ (ኀ) እና (ነ) እንደቅደም ተከተላቸው (በ)፣ (ተ) እና (ቸ) ሆነው ተሸጋሽገዋል፤

፪/ የአዋጁ አንቀጽ ፲፮ ተሰርዞ ከአንቀጽ ፲፯ እስከ አንቀጽ ፵፪ ያሉት ተከታይ አንቀጾች እንደቅደም ተከተላቸው ከአንቀጽ ፲፮ እስከ ፵፩ ሆነው ተሸጋሽገዋል፤

፫/ በአዋጁ አንቀጽ ፴፯ (እንደተሸጋሸገው) ከንዑስ አንቀጽ (፪) ፊደል ተራ (ለ) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ፊደል ተራ (ሐ) ተጨምሯል፡-

"ሐ) የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን፡፡"

፬/ የአዋጁ አንቀጽ ፴፯ (እንደተሸጋሸገው) ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች (፫) እና (፬) ተተክተዋል፡-

"፫/ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ኤጀንሲ ተጠሪነት ለፌደራልና አርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር ይሆናል፡፡

፬/ የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ይሆናል፡-

ሀ) የፍትሕና የሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስትቲዩት፤

ለ) የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን፡፡"

፫. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሚያዚያ ፳፬ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**



1/ Paragraphs (j) and (k) of sub-article (1) of Article 14 of the Proclamation are deleted the subsequent paragraphs (l), (m) and (n) are re-organized as paragraphs (j), (k) and (l), respectively;

2/ Article 16 of the Proclamation is deleted and the subsequent Articles from Article 17 to 42 are renumbered as Articles 16 to 41;

3/ Paragraph (c) is added following paragraph (b) of sub-article (2) of Article 37 of the Proclamation (as renumbered)

"c) the Ethiopian Federal Police Commission."

4/ Sub-articles (3) and (4) of Article 37 of the Proclamation (as renumbered) are deleted and replaced by the following new sub-articles (3) and (4):

"3/ The Charities and Societies Agency shall be accountable to the Ministry of Federal and Pastoralist Development Affairs.

4/ The following executive organs shall be accountable to the Federal Attorney General:

a) the Justice and Legal System Research Institute;

b) the Federal Prison Commission."

3. <u>**Effective Date**</u>

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 2nd day of May, 2016.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**